ለማካሄድ መሞከርም አገሪቱን ወደ ባሰ ከቁጥጥር ውጭ ወደሆነ የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ሊያስገባት ይችላል የሚል ከፍተኛ ስጋት አብሮነት አድሮበታል። ይህንን ነባራዊ ሁኔታ በመሳኝ መልኩ ቀያሪ አገሪቱን ወደ መጥትሬዊ ዴሞክራሲ የማሸጋገር ብቃትም ሆነ ፍላጎት አሁን በስልጣን ላይ የሚገኘው መንግስት እንደሌለውም አብሮነት ይገነዘባል።

ስለሆነም- አገራዊ ምርጫ ማካሄዳችን ለተወሰነ ጊዜ እንዲራዘምና እንደ አገር ሰላማዊ፣ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ለማካሄድ የሚያስችሉንን ተግባሮች በብቃት ማከናወን የሚያስችለን አንድ የእርቅና የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም ጥሪያችንን በድጋሚ እናቀርባለን። ይህ የዕርቅና የሽግግር መንግስት ለምንና እንዴት መቋቋም እንዳለበትም መንግስትና የፖለቲካ ሃይሎች ተገናኝተው መወያየትና መደራደር በአስቸኳይ መጀመር እንዳለባቸው አጥብቀን እናሳስባለን።

በመጨረሻም፤- አገራችን በአሁኑ ወቅት እጅግ አሳሳቢ የሆነ የብሄራዊ ደህንነት ስጋት ውስጥ እንደምትገኝ ተገንዝበን፤ ይህ ስጋትም ያለ ዜጎች ተሳትፎ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሊቀለበስ እንደማይችል አውቀን፤ የአገር ደህንነት የሚያሳስበን ዜጎች ሁሉ አብሮነትን በሁለንተናዊ መልኩ በመደገፍ ተሳትፎ እንድናደርግ ጥሪያችንን በዚህ አጋጣሚ እናቀርባለን።

አብሮነት ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ አንድነት ( አብሮነት)

ጥር 20/ 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ